# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የሀገር ልማት ጠንቆች!

ኤሌክትሪክ ሀገራትን ከድህነትና ኋላ ቀርነት በማላቀቅ በኩል ቁልፍ ሚና የመጫወት አቅም ያለው አስደማሚ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤት ነው:: ኢትዮጵያ ሀገራችንም ዜጎቿን ከጨለማ ለማላቀቅ፣ ኢንዱስሪዎቿን ለማስፋፋት፣ የአገልግሎት ዘርፎቿን ለማዘመን፣ በጥቅሉ "ኤሌክትሪክ ከድህነት የመውጫ መንገዴ ነው" ብላ በማመን በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አደረጃጀቶችን ፈጥራ መንቀሳቀስ ከጀመረች ሰነባብታለች። ይህን አገራዊ ተልዕኮ አንግቦ ኃይል የማምረት ሥራ የሚሠራው ደግሞ የያኔው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለስልጣን የዛሬው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ነው::

ውድ አንባቢያን "ዓባይን በጭልፋ እንዲሉ" የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ስለሚያከናወናቸው በርካታ ሥራዎቹ አውርተን ስለማንዘልቀው እያስነበብናችሁ ያለነው ቆንጠር እያደረግን ነው:: ተቋሙ በአሁኑ ወቅት በግንባታ ላይ ያሉትን ሳይጨምር ከተለያዩ ታዳሽ ኃይሎች ህዳሴን ጨምሮ ከ17 በላይ ኃይል ማመንጫዎችን፣ 189 ማከፋፈያ ጣቢያዎችን ገንብቷል:: እንዲሁም 20ሺህ 252 ሰርኪዩት ኪሎሜትር ርዝመት ያላቸው ከፍተኛ የኃይል ማስተላለፊያ መሥመሮችን ዘርግቶ ያስተዳድራል:: ተቋሙ በአንድ በኩል በየጊዜው እያደገ የመጣውን የኃይል ፍላጎት ለማሟላት እየተጋ ቢገኝም በሌላ በኩል ደግሞ የልማት ጠንቅ በሆኑ ቀበኛ እጆች ክፉኛ እየተፈተነ ይገኛል::

ውድ አንባቢያን የዛሬው ጽfከፋችን በኤሌክትሪክ መሠረተልማት ላይ ስለሚፈጸም ስርቆት ያስቃኘናል:: ተቋሙ ከሰሞኑ የተለያዩ ጋዜጠኞችን ያቀፈ አንድ ቡድን ይዞ በተለያየ ቦታ ያሉ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶችን ያስቃኘ የመስክ ጉብኝት አድርጓል::

እኛም በጉብኝታችን ተቋሙን እየተገዳደረ ስላለው፣ አንገብጋቢ ችግርና ዘላቂ መፍትሄ ስለሚሻው የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ስርቆት "አዋጅ! አዋጅ! አዋጅ! ጆሮ ያለው ይስማ፣ የሰማው ላልሰማ ያሰማ" ለማለት ወድደናል::

የጋዜጠኞች ቡድኑ በወርኃ መጋቢት በቀን 20 በዕለተ ረቡዕ መነሻውን አዲስ አበባ፣ መዳረሻውን ደግሞ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች አድርጎ የተንቀሳቀሰ ነበር:: የመጀመሪያ ምልክታው በጉራጌ ዞን ቡታጂራ ቡዒ አካባቢ የተዘረጋውን የከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ነበር:: ቀጥሎ በወላይታና ዳውሮ ዞኖች መሀል ባለው የኦሞ ወንዝ ላይ የተገነባውን የጊቤ ሦስት የውኃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያን እና የወላይታ ሶዶ ኮንቨርተር ስቴሽንን ነው:: በመጨረሻም ዕድሜ ጠገብ የሆኑትን የቆቃ፣ የአዋሽ ሁለትና ሦስት የውኃ ኃይል ማመንጫዎችን እንዲሁም በሀገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን የአዳማ አንድ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያን ነበር::

ለሀገር ልማት ሁለንተናዊ አበርክቶ ባላቸው የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚፈፀሙ የስርቆት ወንጀሎች ምን ያህል ለተቋሙ የህልውና አደጋ እየሆኑበት እንደመጡና ለሥራው ፈታኝ ችግሮችን እየፈጠሩበት እንደሚገኙ በዓይናችን ያየነውንና ከተቋሙ ሠራተኞች የተነገረንን መረጃ እንዲህ አጠናቅረነዋል::

አቶ ከበደ ፉፋ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የማዕከላዊ ሪጂን 3 የማስተላለፊያ መስመሮች ጥገና ሥራ አስኪያጅ ሲሆኑ ስርቆት ተፈፅሞበት ጥገና እየተደረገለት ስለሚገኘውን የከፍተኛ ኃይል መስመር ተሸካሚ ምሰሶ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውናል:: መስመሩ ከአዳሚ ቱሉ ወደ ቡታጂራ ቡዒ የተዘረጋ ባለ132 ኪሎ ቮልት ኃይል ተሸካሚ ነው:: በዚህ መስመር ላይ በበርካታ የብረት ማማዎች



አቶ ከበደ ፉፋ

ላይ በየጊዜው ስርቆት የሚፈፀም በመሆኑ ማዕከላዊ ሪጂኑ በጥገና ሥራ እንደሚጠመድ ይናገራሉ::

ስርቆት የተፈፀመበትና ጥገና እየተደረገለት የሚገኘው የከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ ተሸካሚ ምሰሶ 89 ተገጣጣሚ ብረቶች ከላዩ ላይ ተሰርቀው ባዶውን ሲታይ "ያ አገር ያለህ!" ያስብላል:: "ገላ በአለባበስ ያምራል" እንዲሉ ማማው ባዶውን ቀርቶ ሲታይ ለተመልካች አይን ይከብዳል::

ምሰሶዎች ሲተከሉ እና ምሰሶውን የሚቀስቱ ብረቶችም እንደየመልክዓምድሩ የየራሳቸው ባህሪ፣ ዓይነትና መጠን ያላቸው መሆኑን የተናገሩት ሥራ አስኪያጁ ከዚህ አንጻር የተሰረቁ ብረቶችን በሌላ ለመተካት ያስቸግራል:: ያም ሆኖ የተሰረቁትን ብረቶች ለጊዜውም ቢሆን በተለያዩ ብረቶች ለመተካት ሲሞከር ብረቶች በሌቦቹ መልሰው የሚወሰዱ መሆኑን ነግረውናል::

የሚያስገርመው ነገር ይላሉ አቶ ከበደ በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ስርቆት መቀነስ እንዲቻል የማያያዣ ብሎኖቹ እንዲበየዱ ቢደረጉም ዳግም በመጋዝ እየተቆረጡ ስርቆት የሚፈጸምባቸው መሆኑ ነው:: ይህም የችግሩን አሳሳቢነት የከፋ ስለመሆኑ ማሳያ ነው ብለዋል::

ስርቆቱ በብረቶቹ ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን ለመረጃ ማስተላለፊያነት በሚውሉ የኮሙዩኒኬሽን መስመር ሳጥኖች ላይ ጭምር ነው:: የሚሰረቁ ዕቃዎችን አሟልቶ አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ በኩል እያደረገ ያለው የገንዘብ፣ የጊዜ እና የጉልበት ወጪ ኪሳራን እያስከተለበት ነው:: ለአብነት ያህል አንድ ባለ132 ኪሎ ቮልት መስመር ተሸካሚ የብረት ምሰሶ ቀደም ባለው ባለው ዋጋ እስከ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር በላይ ከውጭ ሀገር ተገዝቶ የሚመጣ ነው:: በአሁኑ ገበያ ደግሞ ዋጋው በጣም እንደጨመረ ተናግረዋል:: በጥገና ሥራው ተቋሙ ላላስፈላጊ ወጪ እየተዳረገ እንዳለ ገልጸዋል::

የኤሌክትሪክ ኃይል ሲቋረጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሁሉም ሰው ተጎጂ ይሆናል ያሉት አቶ ከበደ ይህ የስርቆት ወንጀል ለተቋሙ ብቻ ሳይሆን ለሀገራዊ ዕድገታችን ከፍተኛ አደጋ የሚፈጥር ነው:: በመሆኑም በአንዳንድ አካባቢ የተጀመሩ የወንጀል ክትትል ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው:: በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ የሀገር ልማት ጠንቅ የሆኑ ሌቦችን "እጅ ከፍንጅ አልተያዙም" በሚል ሲለቀቁ ይታያል:: አጥፊዎች ተገቢው የህግ ማጣራት ሥራ ተሰርቶ አስተማሪ የሆነ ሕጋዊ ቅጣት ሊጣልባቸው ይገባል ሲሉ አቶ ከበደ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል::

ለዛሬ በዚሁ እናብቃ ቀጣይ ሳምንት በወላይታ ሶዶ አካባቢ ስለተፈጸመው ተመሳሳይ ስርቆትና መስተዳድሩ ስለወሰዳቸው አስተማሪ ቅጣቶች የምናስነብባችሁ ይሆናል:: ቸር እንሰንብት!

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ